የሰ/መ/ቁጥር፡- 242504
ሰኔ 28 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

አመልካች፡- አበረ መለሰ

ተጠሪ፡- የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች የካቲት 03 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የባህርዳርና አከባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 3676፤ ጥቅምት 15 ቀን 2015ዓ.ም አመልካች በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ሊነሳ አይገባም በማለት የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ በወንጀል ጉዳይ በሌለሁበት ታይቶ የተሰጠ ውሳኔ ይነሳልኝ በሚል የቀረበን ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ አመልካችን ጨምሮ በሌሎች ተከሳሾች ላይ ሁለት የወንጀል ክሶች ያቀረበ ሲሆን አንደኛው ክስ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1/ሀ) ፤539(1) ድንጋጌን በመተላለፍ የአሁኑ አመልካች ከሌሎች ተከሳሾች ጋር በመሆን ሰው ለመግደል አስቀድመው በማሰብ በሜጫ ወረዳ ብርሃን ጮራ ቀበሌ ልዩ ስፍራው ነጫነጭ እየተባለ ከሚጠራው ቦታ ነሐሴ 14 ቀን 2008ዓ/ም ከጠዋቱ በግምት 3፡00 ሰአት በሚሆንበት ጊዜ ቡቃያው በሬ የተባለውን ሟች ቀደም ሲል የነበራቸውን ፀብ ምክንያት በማድረግ ቂም በመያዝ ሟች ወደ ገበያ ሲሄድ ከመንገድ ጠብቀው በድንጋይ፣ በዱላ ጭንቅላቱን ከደበደቡ በኃላ በሽጉጥ ተኩሰው ግንባሩን በመምታት የገደሉት በመሆኑ በዋና ወንጀል አድራጊነት ከባድ የሰው ግድያ ወንጀል ፈጽመዋል በሚል ሲሆን፤ በሁለተኛው ክስ ደግሞ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32(1/ሀ) እና 671(2) በመተላለፍ በአንደኛው ክስ በተገለፀው ጊዜ፣ቦታ እና የወንጀል ድርጊት አፈጻጸም ሁኔታ ሟችን ከገደሉ በኃላ ሟች ይዞት የነበረውን 10000(አስር ሺህ) ብር እና ግምቱ 800(ስምንት መቶ) ብር የሚያወጣ ቴክኖ

ሞባይል የወሰዱ በመሆኑ በከባድ ውንብድና ወንጀል ፈጽመዋል በማለት አሻሽሎ ያቀረበውን ክስ የተመለከተው የስር ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች በአድራሻቸው ሊገኙ አለመቻላቸውን በማረጋገጥ በጋዜጣ እንዲጠሩ አድርጓል፡፡ አመልካች በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው ጉዳያቸውን በሌሉበት ታይቶ በሁለቱም የወንጀል ክሶች በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ስር ጥፋተኛ በማለት በ20(ሀያ) ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በሌሉበት ታይቶ በተሰጠዉ የጥፋተኝነትና ቅጣት ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለስር ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ አመልካች ከ2008ዓ.ም እስከ 2010ዓ.ም ባለው ጊዜ በአዲስአበባ ከተማ በቀን ሰራተኝነት ሲሰሩ የነበረ በመሆኑ በወንጀል መከሰሳቸውንም እንደማያቁ፤መጥሪያዉ በአግባቡ ሳይደርሳቸዉ የቀረ መሆኑን በመግለጽ በሌሉበት የተሰጠዉ ዉሳኔ ተነስቶ ጉዳዩ ባሉበት እንዲታይ ጠይቀዋል፡፡ የስር ፍ/ቤትም በአመልካች አቤቱታ ላይ ተጠሪ የአመልካች አቤቱታ በማስረጃ የተደገፈ ስላልሆነ ውድቅ ሊሆን ይገባል በሚል አስተያየት ከሰጠ በኃላ በአመልካች በኩል የተቆጠሩት ምስክሮች ሰምቶ ወንጀሉ የተፈፀመው ነሀሴ 14 ቀን 2008ዓ.ም ሲሆን አመልካች ወደ አዲስአበባ መቼ እንደሄዱና አዲስአበባ የነበሩ ስለመሆኑ በዝርዝር እና ታማኝነት ባለው ሁኔታ ስላላስረዱ የምስክርነት ቃላቸው እምነት የሚጣልበት ባለመሆኑ ፍርድን ለማስነሳት በቂ ማስረጃ ሆኖ አልተገኘም በማለት የአመልካች አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የባህርዳርና አከባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 03675፤ በቀን 15/2/2015ዓ.ም ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች ለዚህ ሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም ይህንኑ ብይን በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘት፡- የስር ፍርድ ቤት አመልካች ወንጀሉ ተፈፀመ ከተባለበት ቀን በፊት ጀምሬ አዲስአበባ ከተማ በቀን ሰራተኝነት ስሰራ የነበረ መሆኔን በምስክሮቼ አስረድቼ እያለ በቀን ሰራተኝነት የሚተዳደርን ሰው በወንጀል መከሰስህን በጋዜጣ አይተህ መቅረብ ነበረብህ በሚል ፍርዱ ሊነሳ አይገባም መባሉ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 20(4) ስር የተመለከተዉን የቀረበብኝን ክስ በችሎት ተገኝቼ የመከላከል መብቴን የሚነፍግ ነው፤ አመልካች በምስክሮቼ አዲስአበባ ከተማ የነበርኩ መሆኑ በተመሳሳይ አስረድቼ እያለ በተጠሪ በኩል ይህንኑ ሊያስተባብል የሚችል ማስረጃ ባላቀረበበት ሁኔታ የምስክሮች አመሰካከር የቃላት ልዩነት አለው በሚል ብቻ ፍርዱ አለማንሳቱ የመሰማትና የመከላከል መብቴን የሚገድብ መሆኑን፤ ከዚህ ተጨማሪ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በሌለሁበት በ20 አመት ጽኑ እስራት እንድቀጣ ከወሰነ በኃላም ቢሆን ሌሎቹ ተከሳሾች ውሳኔውን በመቃወም እስከ ክልሉ ሰበር ችሎት ተከራክረው የክልሉ ሰበር ችሎት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር በድጋሚ አከራክሮ እንዲወስን ከመለሰው በኃላ አንዱን ተከሳሽ በነጻ እንዲሰናበት ሌሎቹም በ13 አመት እስራት እንዲቀጡ ሲወስን በድጋሚ ተጣርቶ እንዲወሰን ሲመለስ አመልካችን በተመለከተ መጥሪያ እንዲደርሰኝና መከላከያ ምስክሮች እንዲሰሙ አድርጎ ውሳኔ መስጠት ሲገባው በዝምታ በማለፍ ተሸሮ በተመለሰ ውሳኔ እንድቀጣ መደረጌ ነጻ የመባል ህገመንግስታዊ መብቴን የሚጥስ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ብይን ተሽሮ የተሰጠብኝ

የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ ቀሪ ተደርጎ ጉዳዩ አመልካች ባለሁበት እንደገና እንዲታይ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

ይህ ሰበር ችሎት የአመልካች አቤቱታ መርምሮ አመልካች ከባድ ሰው ግድያ ወንጀል እና ከባድ ውንብድና ወንጀል ፈጽመዋል በሚል የቀረበባቸው ክስ በሌሉበት ታይቶ ጥፋተኛ ተብለው በ20 አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ የተሰተው ውሳኔ እንዲነሳላቸው ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ የመሆኑ አግባብነት ከሲቪልና የፖለቲካ መብቶች አለም አቀፍ ቃል ኪዳን (international covenant on civil and poletical rights) አንቀጽ 14(3) መ ስር ራሱ በተገኘበት የመዳኘት፣ ራሱን በግል ወይም በመረጠው ጠበቃ በኩል የመከላከል፣ ጠበቃ ከሌለው የሕግ አመካሪ እርዳታን ስለማግኘት መብቱን የማወቅ፣ ትክክለኛ ዳኝነት የሚያጓድል ሆኖ ሲታይና የገንዘብ አቅሙ የማይፈቅድ ሲሆን ጠበቃ እንዲቆምለት የማግኘት መብት፣ ከወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነስርኣት ቁጥር 123፣125፣160(2) (3)፣ 162፤197 እና 198 የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በሰ/መ/ቁ 104420፣93577፤94227 ከሰጣቸው አስገዳጅ የህግ ውሳኔዎች፣ እንዲሁም ከኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስቱ አንቀጽ 13/2 ድንጋጌ እንዲሆን ከአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ (2) ሸ እና ቁጥር 10(ሐ) አንጻር ተጠሪ በተገኘበት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ተጠሪ በጽሁፍ መልስ በጽሁፍ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ የሰጠዉ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች አዲአበባ ነበርኩ የፍርድ ቤቱ መጥሪያም ሆነ በጋዜጣ የተደረገውን ጥሪ ስለመደረጉ እውቅና የለኝም በሚል ቢከራከሩም የወንጀል ክሱ የቀረበው በአንድ ቤተሰብ አባላት ላይ በሆኑ አምስት ተከሳሾች ላይ በመሆኑ እና የሁሉም ተከሳሾች አድራሻ በአንድ የገጠር ቀበሌ ነዋሪዎች ስለሆኑ የቀረበባቸው ክስ የሚያውቁበት መንገድ አልነበረም ለማለት የሚቻል ካለመሆኑም በላይ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 61፤162፤163 መሰረት በማድረግ በአገራዊ ሽፋን እና ተነባቢነት ባለዉ ጋዜጣ ጥሪ የሚደረገው በጋዜጣ የመጠራት ዓለማው ተከሳሱ በወንጀል ስለመከሰሳቸው ይሰማሉ፣ ያውቃሉ ወይም ያነባሉ የሚል ግምት የሚወሰድ በመሆኑ በዚህ አግባብ በጋዜጣ ተጠርተው ባለመቅረባቸው በሌሉበት የተሰጠው ፍርድ ሊነሳ አይገባም መባሉ በሚል በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት ስለማይቻል ይጽናልን የሚል ነዉ፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በአጭሩ ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔ/ብይን እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘዉ ጭብጥ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

መርምረን እንደተረዳነዉ በዚህ ችሎት ምላሽ ሊገኝ የሚገባው ጭብጥ የስር ፍ/ቤት አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ በቀን ሰራተኝነት ሲሰሩ የነበረ መሆኑን ጠቅሰው የፍርድ ቤቱ መጥሪያም ሆነ በጋዜጣ የተደረገውን ጥሪ ስለመደረጉ እውቅና ሳይኖራቸው መከሰሳቸውን ሳያውቁ በሌሉበት የሰጠው ፍርድ ተነስቶ ባሉበት እንዲታይ ያቀረቡትን አቤቱታ በስር ፍርድ ቤት በምስክሮቻቸው አዲስአበባ ከተማ የነበሩ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርዮ አረጸጸምዓለማአ የገ ለግልም!

ስለመሆኑ አሳማኝ በሆነ ሁኔታ አላስረዱም በማለት አቤቱታቸዉን ዉድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለው ሲሆን ከዚሁ አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በመሠረቱ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 161 የተቀመጠዉ ቅድመ ሁኔታ ተሟልቶ አንድ ክስ ተከሳሽ በሌለበት እንዲታይ ትዕዛዝ ሲሰጥ ነገሩ እንዲሰማ በተቀጠረበት ቀን ተከሳሹ ሳይቀርብ ቢቀር በሌለበት የሚፈረድ መሆኑን የሚገልጽ የመጥሪያ ማስታወቂያ በጋዜጣ እንዲወጣ ፍርድ ቤቱ እንደሚያዝ ወይም ተከሳሹ የሚደርስ መስሎ ከታየዉ መጥሪያዉ የሚደርስበትን ሌላ መንገድ ፍርድ ቤቱ ሊያዝ እንደሚችል በቁጥር 162 ተመልክቷል፡፡ ይህን ሥርዓት ተከትሎና በዚሁ ሕግ ቁጥር 163(3) መሠረት እንደ ማንኛዉም ደንበኛ ክስ ታይቶ ፍርድ የተሰጠ እንደሆነ በሕጉ ቁጥር 197 እስከ 202 በተመለከቱት ምክንያቶች ፍርዱ ዉድቅ እንዲደረግ ተከሳሹ ማመልከቻ ማቅረብ እንደሚችል በቁጥር 164 ተመልክቷል፡፡ የሕጉ ቁጥር 199(ሀ እና ለ) ደግሞ በሌለበት ፍርድ የተሰጠበት ሰዉ ፍርዱ ዉድቅ ተደርጎ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ የሚያቀርበዉ ማመልከቻ የሚፈቀደዉ እንዲቀርብ መጥሪያ ያልደረሰዉ እንደ ሆነ ወይም ራሱ ወይም ጠበቃዉ ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል ምክንያት መቅረብ አለመቻሉን ያስረዳ እንደሆነ ነዉ በማለት ደንግጓል፡፡

"መጥሪያዉ ያልደረሰዉ እንደሆነ" የሚለዉ መስፈርት እንዴት ሊተረጎም ይገባል የሚለዉን ስንመለከት "መጥሪያዉ ያልደረሰዉ እንደሆነ" የሚለዉን መስፈረት በተመለከተ እንደሕጉ አጻጻፍ መጥሪያ የደረሰዉ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ዐ/ሕግ እንጂ ተጠሪ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የሕጉ አጻጻፍ ፍ/ቤቱ መጥሪያ የደረሰዉ መሆኑን ግምት እንዲወስድ ዕድል አይሰጥም፡፡ በሥነ ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 162 የተመለከተዉ የጋዜጣ ጥሪ ጉዳዩን ተከሳሹ በሌለበት ለማየት ጥሪ የማድረጊያ ዘዴ እንጂ ፍርዱ ውድቅ ተደርጎ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ የቀረበዉን አቤቱታ ዉድቅ ለማድረግ የሚያስችል መስፈርት አይደለም፡፡ ተከሳሽ የሆነ ወገን "መጥሪያዉ ያልደረሰዉ እንደሆነ" የሚለዉን መጥሪያ ያልደረሰዉ መሆኑን በማስተባበል ማስረዳት የሚጠበቅበት፤ ግምት መዉሰድ ሳያስፈልግ ዐ/ሕግ ለተከሳሹ መጥሪያ የደረሰዉ መሆኑን በበቂ ማስረጃ ማረጋገጥ ሲችል ብቻ ነዉ፡፡

ከላይ ከተገለጸዉ በተጨማሪ "መጥሪያዉ ያልደረሰዉ እንደሆነ" የሚለዉን መስፈርት ተከሳሽን በሚጠቅም መልኩ በሰፊዉ መተርጎም እና የተከሳሽን የመከራከር መብት የማረጋገጥ ግዴታ ፍ/ቤቶች ላይ የሚጥለዉ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 20 ከተደነገጉት የተከሰሱ ሰዎች መብቶች መካከል አንዱ በንዑስ አንቀጽ 4 የተመለከተዉ የተከሰሰበት ጉዳይ በፍርድ ቤት ሲታይ በችሎት ተገኝቶ የቀረበበበትን ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረበበትን ምስክሮችን የመጠየቅ፣ለመከላከል የሚያስችለዉን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቹ ቀርበዉ እንዲሰሙለት የመጠየቅ መብት አለው ድንጋጌ ነው፤ እንደዚሁም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 9(4) መሰረት ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸዉ አለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ የህግ አካል ሲሆኑ መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶችን በተመለከተም በተግባራዊ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርዮ አረጸጸ ምዓለማአ የገ ለግልም!

አፈፃፀማቸዉም ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸዉ አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ህግጋት፣ አለምአቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነትና አለምአቀፍ ሰነዶች መርህዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ ሊተረጎሙ እንደሚገባ አንቀፅ 13 (1 እና 2) ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ የምንረዳዉ አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ህግጋትና አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሰነዶች መርሆዎችን ከሀገራችን ህግጋት ጋር አጣጥሞ ትርጉም መስጠት የፍርድ ቤቶች ህገ መንግስታዊ ግዴታ መሆኑን ነዉ፡፡ አገራችን ባፀደቀችው ዓለም አቀፍ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ስምምነት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 3/መ ላይም በወንጀል ስለተከሰሰ ሰው ያለው መብት “To be tried in his presence, and to defend himself in person or through legal assistance of his own choosing; to be informed, if he does not have legal assistance, of this right; and to have legal assistance assigned to him, in any case where the interests of justice so require, and without payment by him in any such case if he does not have sufficient means to pay for it;” በሚል የተመለከተው የወንጀል ክስ በሚታይበት ጊዜ ተከሳሽ ራሱ በተገኘበት የመዳኘትና የመከላከል መብት እንዳለው ነው፡፡ ከዚሁ ሕገ-መንግስታዊ ድንጋጌና አለምአቀፍ ቃልኪዳን ሰነድ ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ መርሁ የወንጀል ጉዳዮች ተከሳሽ በተገኘበትና የመከላከል መብቱ በተጠበቀበት የሚካሄድ መሆኑን ሲሆን ተከሳሽ በሌለበት አንድ የወንጀል ጉዳይ የሚታየዉ በልዩ ሁኔታ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 161 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት ቢሆን እንኳ በመርሁ የተቀመጠዉን የተከሳሽን የመከራከር መብት ለማረጋገጥ ሲባል ፍርዱ እንደገና ተነስቶ ጉዳዩ እንደገና የሚታይበት ስርዓት በቁጥር 197 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች የተቀመጠ በመሆኑ በተቻለ መጠን ተከሳሹ በእርግጠኝነት መጥሪያ ደርሶት በችሎት የመገኘትና የመከራከር መብቱን አዉቆ መተዉ እስካልተረጋገጠ ድረስ ይህ መብቱ ሊነፈግ እንደማይገባ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 199 (ሀ) ላይ “መጥሪያዉ ያልደረሰዉ እንደሆነ” በሚል የተቀመጠውን መስፈርት መሠረት በማድረግ ተከሳሹ በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ፍርድ እንዲነሳ ባመለከተ ጊዜ ተከሳሹ በትክክል መጥሪያ ደርሶት የመከራከር መብቱን አዉቆ በመተዉ መቅረቱ አሻሚ ባልሆነ መልኩ ዐ/ሕግ በሚያቀርበዉ በቂ ማስረጃ ካልተረጋገጠ በቀር ማወቅ ነበረበት ወይም ሊያዉቅ ይችላል የሚል ግምት በመዉሰድ ያቀረበዉ ማመልከቻ ዉድቅ ሊደረግ እንደማይገባ በዚህ ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ 165271፤186965፤104220፤93577፤94227 እና በሌሎች የሰበር መዝገቦች አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተሰጠበት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የክስ ማመልከቻውን ለአመልካች ለማድረስ በተደረገው ጥረት አመልካች በአድራሻቸው ተፈልገው ሊገኙ ያልቻሉ መሆኑን የተረጋገጠ ሲሆን በአመልካች ላይ የቀረበው ክስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 161 ላይ በተመለከቱት ሁኔታዎች በሌሉበት ሊታይ የሚችል ከመሆኑ አኳያ ፍ/ቤቱ በቀጣይነት አመልካች ጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግላቸው ትዕዛዝ መስጠቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 162 አግባብ የተሰጠ በመሆኑ በዚህ ረገድ ፍ/ቤቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል ለማለት አይቻልም፡፡ ሆኖም ፍ/ቤቱ

የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ለማድረግ የሰጠው ምክንያት በምስክሮቻቸው አመልካች አዲስአበባ ከተማ የነበሩ ስለመሆኑ አሳማኝ በሆነ ሁኔታ አላስረዱም በማለት በመሆኑ የስር ፍ/ቤት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 162 ተከሳሹ በሌለበት ነገሩ እንዲሰማ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ለመስጠት የሚችልበትን ቅድመ ሁኔታ መነሻ በማድረግ ለአመልካች የጋዜጣ ጥሪ ማስተላለፉ መጥሪያ ይደርሳቸዋል የሚል ግምት ለመውሰድ እንጂ መጥሪያ እንደደረሳቸው ማረጋገጫ አድርጎ የሚወሰድ ባልሆነበት እንዲሁም ተጠሪ የሆነው ዓቃቤሕግ አመልካች ምርመራ እየተጣራባቸው መሆኑን ወይም የወንጀል ክስ የቀረበባቸው ስለመሆኑ እያወቁ የተደበቁ ስለመሆኑ ባላስረዳበት አመልካች ከተከሰሱበት ወንጀል ክብደት አንጻር በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ጉዳዩ ባሉበት እንዲታይ ማድረግ ሲገባው የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን ማመልከቻ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ብይን የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 199(ሀ) ድንጋጌ ይዘትና በሕገመንግስቱ ለተከሰሱ ሰዎች የተጠበቁላቸውን መሠረታዊ መብቶች ያላገናዘበ በመሆኑ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ብይን በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ ሀ እና ሸ) እና ቁጥር 10(1/ሐ) ላይ ከተቀመጡት መመዘኛዎች አንጻር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለው ውሳኔ ተጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የባህርዳር አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 03-03676፤ ሐምሌ 19 ቀን 2009 ዓ.ም አመልካችን በሚመለከት በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ሐምሌ 26 ቀን 2009 ዓ.ም አመልካችን በሚመለከት የሰጠው የቅጣት ውሳኔ እንዲሁም አመልካች ጉዳያቸው ባሉበት እንዲታይ ያቀረቡትን ማመልከቻ ውድቅ በማድረግ በቀን 15/2/2015ዓ.ም የሰጠው ብይን በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ስነ- ስርኣት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1/ለ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የባህርዳር አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት አመልካች በሌሉበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ ጉዳያቸው ባሉበት እንዲታይ ያቀረቡትን ማመልከቻ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው በማለት ክርክሩ አመልካች ባሉበት ጉዳያቸው እንዲታይ በማለት ወስነናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ተመላሽ ይደረግ፡፡

ፍ/ደ　　　　　　　　　　　　የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ

አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አይገለግልም!